


# ታላቅ የምስራች ለኢትጵያ ሕዝብ!!

**06 /04/2009**

በኢትዮጵያ ሕዝብ ትከሻ ላይ የተጫነዉን ፋሽታዊ ሥርዓት በመደምሰስ ነጻነት፤እኩልነት፤ ፍትህና አንድነት የሰፈነባት ዴሞክራያዊት ኢትዮጵያ እንድትገነባ የሕይወትና የደም መስዋዕትነት በመክፈል ላይ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የጀመረዉን ፈታኝ ትግል በድል ለማጠናቀቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ የትግል አድማሱን እያሰፋና እያጠናከረ በመሄድ ላይ ነዉ። ግንባሩ በአዉደ ግንባር የሚያከሂደዉን የትጥቅ ትግል እያፋፋመ በጠላት ላይ ተደጋጋሚ ወታደራዊ ድሎችን በመጎናጸፍ ላይ ሲሆን፤ በተጎዳኝም ለሁለገብ ትግሉ አጋዥ የሆኑ ፓለቲከዊ፤ድርጅታዊና አስተዳደራዊ እርምጃችን በመዉሰድ ላይ ይገኛል።

የሕዝብ ንብረት የሆኑትና ለሕዝብ የተሟላ መረጃና ትምህርት መስጠት የነበረባቸዉ  የመንግስት መገናኛ አዉታሮች የፋሽስታዊ ወያኔ አደንቋሪ ፐሮፓጋንዳ ማስተላለፊያ አሽንዳች በመደረጋቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትክክለኛ የመረጃ አገልግሎት ማግኘት  አልቻለም። ለይምስል አለ የሚባለዉም ነጻ ፐሬስ በሚደርስበት ወከባና አፈና አማራጭ የህዝብ ድምጽ ለመሆን ያለዉ ዕድል ተዝግቷል። ይህ ሁኔታ እስካልተለወጠ ድረስ ትግሉ የተሟላ ሊሆን ስለማይችል አማራጭ መንገድ መፈልግ ግድ ይላል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በማካሄድ ላይ ያለዉን ወታደራዊ ፍልሚያ በፐሮፓጋንዳ ሥራ ለማገዝና የአርበኛዉን ተጋድሎ ደጀን ለሆነዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤የሕዝብን ብሶትና ትግል ለአርበኛዉ በማሰራጨት እንደ ድልድይ ሆኖ ለማገልገልና  እንደዚሁም በሀገራችን የሚፈጸመዉን መጠነ-ሰፊ ግፍና የስብአዊ መብት ረገጣ በማጋለጥ የሥርኣቱን ብሉሽነት ለዓለም ማህበረሰብ ለማሳወቅ የሬዲዮ ስርጭት ፐሮግራም ለመጀመር ዝግጅቱን ያጠናቀቀ መሆኑን ለታላቁ ኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለታጋዩ አርበኛና ደጋፊቹ ሲያበስር በታላቅ ደስታ ነዉ።

**ይህ «የአርበኛ ድምጽ ሬዲዮ» በመባል የሚታወቅ የሬዲዮ ሥርጭት በሳምንት አራት ጊዜ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፍ ሲሆን፤ የሥርጭቱም ፐሮግራም ዘወትር ማክሰኞ ከቀኑ 3 ሰዓት እስከ 3.30፤ ከምሽቱ 1 ሰአት እስከ 1.30፤ ቅዳሜ ከቀኑ 3.00 ሰዓት እስከ 3.30 ሰአትና ከምሽቱ 1 ሰአት እስከ 1.30 በ60 ሜትር ባንድ አጭር ሞገድ ወይም በ5006 ኪሎህርዝና በ 1089 መካከለኛ ሞገድ የሚያስተላለፍ መሆኑን በቅድሚያ ያስታዉቃል።**

## አንድነት ሃይል ነው!!
## የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

Email: info@eppfonline.org:        Website:  www.eppfonline.org